የምዕራብ ጐጃም ዞን አስተዳደር መቀመጫ በክልሉ መንግስት ውሣኔ ወደ ፍኖተ ሠላም እንዲዛወር በመደረጉ ምክንያት ባህር ዳር ላይ ያስችል የነበረው የዚሁ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያስተናግዳቸው የነበሩትን የፍትሐብሄርና የወንጀል ጉዳዮች በሙሉ ወደ ፍኖተ ሠላም ማዛወር በፍትህ አገልግሎቱ ተደራሽነት ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ እስካሁንም ድረስ የፍርድ ቤቱን ሰፋ ያለ ክፋይ እዚሁ በሥራ ላይ ለማቆየት ቢሞከርም ሁለቱን ክፍሎች በተለያዩ ርቀቶች ለመከታተል የተደረገው እና የሚደረገው ጥረት ለጋራ አስተዳደራዊ ምሪት የሚከብድና ለከፍተኛ ወጭ የሚዳርግ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከባህር ዳር ከተማ እና አካባቢዋ የሚመነጩትንና በስራ ላይ ባሉት የባህር ዳር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የማይወድቁትን መደበኛ የፍትሐብሄር እና ወንጀል ጉዳዮችን ለዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነት ሲባል በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ ስርዓት ተቀብሎ የሚዳኝ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጀት በማስፈለጉ

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 1/3 ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## 1. ?? ? ???

ይህ አዋጅ “የባህር ዳር ከተማና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር----210/2006 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

WHEREAS, it has been found heavy to direct (manage) jount administration activiity and it exposes to high expenditure; that make and shall make effort, to follow up the two parts by different distances; Not withstanding still now tried to implement the wide part of the court’s activity here in Bahir Dar; to minimise the negative impact of accessibility of the justice service; transfering completely the vivil and criminal cases of the high court, that it executes in Bahir Dar to Finoteselam; due to, the place of the western Gojjam Zone Administaration is transfered to Finote selam. by the decision of the Regional Government;

WHEREAS, it has been found necessary to organize high court, accepting with first stage, as well as, with appeal system; in order to access judicial service of the regular civil and criminal cases, stipulated or seen under the power of the Bahir Dar city courts, found in effect ; and, shall be initiated from Bahir Dar city and its surrounding;

THEREFORE, Pursuant to Article /49/ sub-article 3/1/of the Revised National Regional Constitution, vested with its power, the Council of Amhara Region issued this Proclamation.

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as “ the Amhara National Regional State of Bahir Dar and its Surrounding High Court Establishment Proclamation No.210/2014

## 2. ??? ??? ? ?? ??

1. የባህር ዳር ከተማና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት /ከዚህ በኋላ "ፍርድ ቤቱ" እየተባለ የሚጠራው አካል/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. ፍርድ ቤቱ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 11/1988 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቋም ያለው ሲሆን ተጠሪነቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

## 3. ?? ??? ?? ???? ????

1. ፍርድ ቤቱ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 11/1988 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 5 መሠረት በግልጽ ተለይተው በፌደራሉ መንግስት ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር ከሆኑት እና በተሻሻለው የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ከተሞች እንደገና ማቋቋሚያ፣ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ መሠረት በተቋቋሙት የከተማ ነክ ጉዳይ ተመልካች ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር ከሚወድቁት ጉዳዩች በስተቀር በክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 62 እና 63 ስር የተመለከቱትን የዳኝነት ተግባራት ሁሉ የማከናወን ስልጣን ይኖረዋል፤

## 2. Establishment and Accountability

1. The Bahir Dar and its surrounding high court /hereafter/ caved court is established by this proclamation;
2. The court, pursuant to sub-article /2/ of Article /3/ as /amended/ the Amhara National Regional State courts Establishment proclamation No. 11/1996, has a structure of the zone high court, shall be accountable to the supreme court of the Region.

## 3. Judicial Power of the Court

1. The court, pursuant to Article 5 of the Amhara National Regional State Courts Establishment Proclamation No 11/1995 E.C /as amended/, shall have a power to perform all judiciary activities stipulated, under Article 62 and 63 of the Regional constituion, with the exception of cases, these are isolated clearly; under the federal govenment courts and with the Revised Natonal Regional State urbans Re- amendement establishment, organizational and power and duties determination proclamation No. 91/2004 /as ameded/, with the established urban issue concern courts;

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ፍርድ ቤቱ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 11/1988 ዓ.ምን እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 169/2002 ዓ.ም አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥር “ሀ” 6/1 ስር እንደተመለከተው በፍትሐብሄርና በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓትም ሆነ በሌሎች ህጐች በተደነገገው መሠረት ባህር ዳር ከተማ፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ ይልማና ዴንሳ፣ ጐንጅ ቆለላ፣ ሜጫ፣ ሰሜን አቸፈር እና ደቡብ አቸፈር ወረዳዎች ክልል የሚቀርቡለትን የፍትሐብሄርና የወንጀል ክሶች በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ ተቀብሎ የማየትና ፍርድ የመስጠት ስልጣን አለው ፡፡

## 4. ?? ??? ?? ?? ??? ???

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 11/1988 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ /2/ ስር የተደነገገው ቢኖርም፤ ፍርድ ቤቱ በመደበኛነት የሚያስችለው በባህር ዳር ከተማ ይሆናል ፡፡

## 5. ???? ? ?????? ??? ? ??

በፍትሐብሄርም ሆነ በወንጀል ረገድ ፍርድ ቤቱ የሚኖረውን የሥልጣን ክልል፣የችሎቶች አደረጃጀት፣የዳኝነት ሥራ አካሄድና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዩች በሚመለከት አግባብ ያላቸው የአዋጅ ቁጥር 11/1988 ዓ.ም /እንደተሻሻለና የአዋጅ ቁጥር 169/2002 ዓ.ም ድንጋጌዎች በተመሣሣይ ይሠራባቸዋል ፡፡

2. Without Prejudice to, the general provision stipulated under sub –article /1/ of this Article, the Court of Amhara National Regional State courts establishment proclamation No. 11/1995; /as amended/ issued proclamation No. 169/2010, stipulated under Article 2 “a” 6/1, pursuant to the provision of the civil and criminal procedure as well as, by other laws; shall have a power to see and decide the submitted civil and criminal charges by the firs Stage ,as well as , appeal; in the region of Bahir Dar city, Surrounding of Bahair Dar, yilmana Denca, Gonjikolela, Miecha, North Achefer and South Achefer woredas.

## 4. Place of Hearing of the Court

Notwithstanding the provision stipulated under sub-apticle /2/ of Artcle /8/ of the Amhgara National Regional State Courts Establishment Proclamation No. 11 /1996 /as amended/, the court shall hearing regularly, in Bahir Dar Town.

## 5 . Working with Related Provisions

Pursuant to civil,as well as, crime, the courts shall have jurisdiction organizational of Hearings way of judiciary activities and other related cases, the approproate proclamation No. 11/1996/as amended/ and proclamation NO 169/2010, Provisions similar are in effect.

## 6. ?? ? ?? ?? ??? ????

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የባህር ዳር ችሎቶች ተጀምረው በመታየት ላይ ያሉ የፍትሐብሄርም ሆነ የወንጀል ጉዳዮች አዲስ ወደ ተቋቋመው የባህር ዳር ከተማና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዛውረው ይጠናቀቃሉ ፡፡

## 7. ??? ?? ???? ??

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሰት ዝክረ- ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር

መጋቢት 1/2006 ዓ.ም

ገዱ አንዳርጋቸው

የአማራ ብሄራዊ ክልል ኘሬዘደንት

## 6. Pending Cases

Pending cases prior to the coming into force of this proclamation; the civil, as well as, the criminal cases that are commenced in Bahir Dar Hearings, of the court of western Gojjam, shall be accomplished, transfered to the newly established, Bahir Dar and its surroundings High court.

## 7. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of its publication in the Zikere –Hig Gazzeettee.

Done at Bahir Dar,

This 10th day of March, 2014

Gedu Andargachew

President of the Amharа National Region